# ታጥበውም አይጠሩ

የደርግ የወያኔ ፤ የወሬ ፋብሪካ
ዲስኩሩን በሳይበር ፤ ሸርክቶ ሲከካ
በገብሩ በስዬ ፤ የጎጥ ፖለቲካ
ወያኔ . . አቦል  ሆኖ ፤ አረና በረካ
እያነፈነፈ ፤ በመጣበት ዱካ
ስልቻን አንስቶ ፤ ቀልቀሎ ሊተካ
አልሸሹም . . ዞር አሉ ፤ ያራዳ ትረካ ።

ታጥቦ የማይጠራ ፤ መፍትሄ የሌለው
የበሽታ ክፉ ፤ ያንጎል . .እከክ ያለው
ለወያኔ ውርዴ ፤ መች . .መድህኒት አለው ።

የዚያች ላም ፤ ጥጃ . . አብረው የመከሩ
በጎሳ በቋንቋ ፤ አርደው የመተሩ
ኢትዮጵያን  ሸንሽነው ፤ ገለው የቀበሩ
በአረና መድረክ ፤ ስዬ . . ቢሉ ገብሩ
ዛሬም ዘረኝነት ፤ አንድ ነው . . መዝሙሩ
በተቃጠለ ፊልም ፤ ግርግር መፍጠሩ
የወያኔ አሻጥር ፤ የደቀመዝሙሩ
የደደቢት ሥራ ፤ መች ጠፋን . . ሚስጥሩ ።

በወንፊት ተነፍተው ፤ ዳግም ቢበጠሩ
ፈትገው ቢያሿቸው ፤ ምን ቢንጠረጠሩ
በደም የጨቀየን ፤ መኳል መሞሸሩ
ዛሬም አንሸወድ ፤ ይብቃ ግርግሩ
አረናም መድረክም ፤ ይጨሁ ያጓሩ
ሸንፍላዎች ናቸው ፤ ታጥበውም አይጠሩ ።

ታዛቢው ... March, 15, 2010